# የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ አገር-ወዳድና ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች እና ኢሕአዴግ፤ ከዚኽ ወዴት?

*ከአያል ሰው ደሴ፤- የግል አስተያየት*

***ክፍል አሥራ-ሰባት** (ከክፍል አሥራ-ስድስት የቀጠለ)፤-..*

**ኢዴኃኅ....**

በኅብረቱ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት "የዚኽ ምክር ቤት አባላት ካላቸው የዕድሜ፣ የሥራና የትምሕርት ሠፊ ልምድና እውቀት አንዳንድ ባህላዊ ግጭቶችን ለማስወገድና ማናቸውንም ብሔራዊ ጠቀሜታ ያላችውን አሳቦች ለኅብረቱ አመራር ይጠቁማል፣ ያማክራል፣.." ".. በልዩ ልዩ የኅብረቱ እርከኖች ለመፍታት ያልተቻሉ ጉዳዮች በኅብረቱ የሥራ-አመራር ወይም የሥራ-አስፈጻሚ ኮሚቴ አማካይነት ሲተላለፉለት ጉዳዮችን ይመረምራል፣ መፍትኄ ይሰጣል".. "... ለሥራው ቅልጥፍና በሚያመቸው መልክ በአገር-ውስጥና ከአገር-ውጭ በሁለት ክፍሎች ሆኖ በአንድ መመሪያ ሊሠራ ይችላል" ይላል፡፡ እያንዳንዱ የኅብረቱ አባል ድርጅት አንድ፣ አንድ ሰው በማቅረብ በሁሉም አባል ድርጅቶች ተቀባይነት ያላቸውን፤ ቢያንስ ከማንኛውም አባል ድርጅት ተቃውሞ ያልቀረበባቸውን፣ እንደ ልጅ ሚካኤል እምሩ፣ ኮ/ል አስናቀ እንግዳ፣ ሎሬት ፀጋዬ ገ/መድኅን፣ አቶ መሐመድ አመዴ፣ ዶ/ር ማይገነት ሽፈራው፣ ወዘተ... የመሣሰሉ በአገሪቱ ያሉ ታዋቂ፣ ለኅሊናቸው ተገዥ ናቸው ብሎ ያመነባቸውንና የማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት አባል ያልሆኑ አሥራ-አምስት ኢትዮጵያውያንን በ"አማካሪ ምክር-ቤት" አማካይነት አደራጅቶ የመዋቅሩ ዘርፍ ሲያደርግ፣ ተግባራቸውና ሚናቸው በኅብረቱ ውስጥ የሚከሰቱ ችግሮችን በሽንግልና እያዩ በመሸምገል ላይ ብቻ የተገደበ ሣይሆን ይግባኝ የሌለው ብይን የመስጠትም ኃላፊነት ጭምር እንዳላቸው እና ሁሉም በብይናቸው ለመገዛት ዝግጁ መሆኑን አምኖና ተቀብሎ ነበር፡፡ አልፎም አማካሪ ምክር-ቤቱ ለአገርና ለሕዝብ አንድነት፤ ለሰላምና ለእድገት አስፈላጊ የሆኑ አሳቦችንና ምክሮችን ለኅብረቱ በማስተላለፍ በአጠቃላይ የኅብረቱ አባላት በውዴታ የመሠረቱት ድርጅት አንድነቱን ጠብቆ፣ መሪዎችም የተጣለባቸውን ኃላፊነት በብቃትና በጥንቃቄ እንዲወጡ ታዛቢ፣ መካሪና ሽምጋይ በመሆን እንዲሠሩ ለማድረግ ተሞክሯል፡፡

ይኽንን በማድረግም፣ ማለት በአንድ በኩል የአገሪቱን ምሑራን የግድ የድርጅት አባል መሆንን በማይጠይቅ መልኩ ምሑራዊና ሙያዊ ተክኅሎቻቸውን አገራቸውንና ሕዝባቸውን በሚጠቅም መልኩ ሥራ ላይ ለማዋል ያላቸው በጎ አመለካከት እውን እንዲሆን ዞሮ-ዞሮ እውቀታቸውንና ምኞታቸውን በተግባር መተርጎም ለሚኖርባቸው የፖለቲካ ድርጅቶች በግልጥና በሥርዓት ማስተላለፍ የሚችሉበትን መሥመር በማበጀት፣ ጥናቶቻቸውንም በልዩ ልዩ ሕዝባዊ ስብሰባዎች ላይ በማቅረብ ውይይት እንዲደረግባቸውና ኅብረቱም ይሁን ሌሎች ድርጅቶች ወደ-ፊት ለአገር ይጠቅማሉ ብለው የሚነድፏቸው መርኃ-እቅዶች (ፖሊሲዎች) ከላይ ዝም ተብሎ በሕዝብ ላይ የሚጫኑ ሣይሆኑ ዜጎች አስተያየቶቻቸውን የሰጡባቸው፣ ግልጥ መረዳትና መግባባት ላይ የተመሠረቱ፣ ቢቻልም ብሔራዊ-መግባባት ያገኙ እንዲሆኑ ለማድረግ 'የጥናትና ምርምር' አካል በማቋቋም ትግሉ ምሑሩን ያላገለለ ብቻ ሣይሆን በሥርዓት ያቀፈና ተሣታፊ ያደረገ እንዲሆን ማመቻቸቱ፣ በሌላ በኩል በድርጅቶች መኻል የሚነሱ ያላስፈላጊ አተካራዎችን በውጭ-አገር ሽምጋዮችና አደራዳሪዎች አማካይነት ሣይሆን ነገሮችን በኢትዮጵያዊ ዓይን በሚያዩ አገር-በቀል ዜጎች አማካይነት እንዲታዩና መፍትኄ እንዲገኝ ለማስቻል ታዋቂ ኢትዮጵያውያንን በአማካሪ ምክር-ቤት በማካተት የመዋቅሩ አካል ማድረጉ ኢዴኃኅ (ኅብረቱ) ለቆመበት ለአገራችን የሥዓት ለውጥ-አስገኚ ራዕይ የሚያደርገውን ሕዝባዊ ትግል በአዲስ ሁሉን-አቀፍ አሠላለፍና መንፈስ በቁርጠኝነት እንደተሠለፈ የሚያሣይ ነበር ማለት ይቻላል፡፡

ሠ-1) *የአመራር አካላትና የኃላፊዎች ስያሜ፤* ይኽ ጽሑፍ ቀደም-ያሉ ተሞክሮዎችን

በአጭሩ በመቃኘት አንዳንድ ልምዶች ለወደ-ፊት የጋራ ጥረቶች አስተዋፅዖ ሊኖራቸው ይችላል ከሚል እሳቤ የቀረበ በመሆኑ በሂደት የተስተዋሉ ዝርዝር ጉዳዮች ውስጥ መግባት ዓላማው አይደለም። ሆኖም በኅብረቱ ላይ ይሰጡ ከነበሩ አንዳንድ የተዛቡ አስተያየቶች ውስጥ አመራርን በተመለከተ አንዱ ክፍል ስለ-ነበር ዞር-ብሎ በመጠኑ መቃኘቱ ያላስፈላጊ ብዥታን ሊያስወግድ ይችላል የሚል ግምት ስላለኝ፣ በአጭሩ እነሆ።

በመሥራች ጉባዔው ላይ ከተወሰኑ ጉዳዮች አንዱ ሁሉም የጉባዔው አባላት በሙሉ ስምምነት ለፈጠሩት ኅብረት (ኢዴኃኅ) ያላቸውን የጋራና የተናጠል ኃላፊነትና ግዴታ በሚገባና በግልጥ ተረድተው የሚጠየቅባቸውንና የሚጠበቅባቸውን ሁሉ በብቃት ለመወጣት እንዲችሉና ያላስፈላጊ አለመግባባቶችን በሰከነና በዴሞክራሲያዊ መንገድ ለማስወገድ እንዲረዳ ሁሉም በደንብ የተረዳውና የሚቀበለው 'የሥነ-ምግባር መመሪያ' መኖሩ እንዳለበት አጠያያቂ አልነበረም። ስለሆነም ሁሉም የሚመራበትና እንዲያከብረውም የሚጠበቅበት 'የሥነ-ምግባር መመሪያ' በንባብ ተደምጦ ጉባዔው ተቀብሎ አፅድቆታል። የጉባዔው የመጨረሻ መቋጫ የስብሰባ ነጥብ (አጀንዳ) የነበረው ሁሉም የተግባቡበት አገራዊና ሕዝባዊ ራዕይ በተስማሙበት የትግል ስልት ተግባራዊ መሆን እንዲችል ያፀደቁትን መዋቅር ተከትሎ የልዩ ልዩ ዘርፍ አመራር-ሰጪዎችን በምርጫ መሰየም ነበር።

ቀደም-ሲል እንደተገለጠው በመዋቅሩ መሠረት በጉባዔው ተሣታፊ የሆኑት ድርጅቶች ሁለት፣ ሁለት ተወካዮችን መድበው በጠቅላላው ሰላሣ አባላት ያሉት 'ብሔራዊ ምክር-ቤት'፣ ከነዚኽ ውስጥ አንድ፣ አንድ አባላት የሚወከሉበት አሥራ-አምስት አባላትን ያቀፈ 'ሥራ-አስፈፃሚ ኮሚቴ' (በእያንዳንዱ ተጨማሪ ድርጅት ሁሉም የኅብረቱ መዋቅራዊ ዘርፎች በተመጣጣኝ ቁጥር ይጨምራል) እና በብሔራዊ-ሸንጎው የሚመረጥ 'ማዕከላዊ አመራር' ሲኖረው በጎኑ 'አማካሪ-ምክር ቤት' እና 'የቁጥጥርና ክትትል (ኦዲትና ኢንስፔክሽን)' ኮሚቴዎች፣ ከሥሩ ደግሞ ልዩ ልዩ የተግባር ኮሚቴዎችና አካላት አሉት። በጉባዔው የመጨረሻ ቀን ስብሰባ ላይ ብሔራዊ ሸንጎውና ሥራ-አስፈፃሚ ኮሚቴው ከተሰሙ በኋላ ማዕከላዊ-አመራሩን ገለልተኛ አስመራጭ ኮሚቴ በማቋቋም በዴሞክራሲያዊ ምርጫ ሰይሟል። (በወቅቱ ማዕከላዊ-አመራሩ አንድ ሊቀ-መንበር፣ ሁለት ምክትል ሊቀ-መናብርት፣ አንድ ዋና-ፀሐፊ፣ አንድ ምክትል ዋና-ፀሐፊ እና አንድ እረዳት ዋና-ፀሐፊ በድምሩ ስድስት አባላት በምርጫ ተሰይመዋል። ከስድስቱ ማዕከላዊ-አመራር አባላት ውስጥ አራቱ (ሊቀ-መንበሩ፣ ምክትል ሊቀ-መንበሩ፣ ዋና-ፀሐፊውና ረዳት ዋና-ፀሐፊው) ተቀማጭነታቸው በአገር-ውስጥ በዋና ጽ/ቤቱ ሲሆን፣ ሁለቱ (አንዱ ምክትል ሊቀ-መንበርና ምክትል ዋና-ፀሐፊው) ኅብረቱን በውጭ በመወከል ከአገር-ውጭ ያለውን የኅብረቱ እንቅስቃሴ የማስተባበር ኃላፊነት ነበረባቸው። ሆኖም በኅብረቱ የመጀመሪያ ጉባዔ ላይ በአገር-ውስጥ ላለው አመራር አንድ ተቀዳሚ ምክትል ሊቀ-መንበር፣ በውጭ-አገር ደግሞ የአውሮጳ ቅርንጫፍ ጽሕፈት-ቤትን በማቋቋም አንድ ምክትል ሊቀ-መንበርና አንድ ምክትል ዋና-ፀሐፊ በምርጫ በመሰየም ቁጥሩ ወደ-ዘጠኝ ከፍ እንዲል ሆኗል)።

በዚኽ መሠረት በቅድሚያ በአገር-ውስጥ ለሚገኘው የኅብረቱ ዋና ጽ/ቤት የሚመደቡት የአመራር አባላት (ሊቀ-መንበር፣ ምክትል ሊቀ-መንበር፣ ዋና-ፀሐፊ እና እረዳት ዋና-ፀሐፊ) የሚመረጡት መቀመጫቸው በአገር-ውስጥ ከሆኑ ድርጅቶች ውስጥ ለሥራ-አስፈጻሚው አካል ከተመደቡት መኻል ስለሆነ እያንዳንዱ ድርጅት ለእያንዳንዱ የኃላፊነት እርከን ይሆናል የሚለውን በአስመራጭ ኮሚቴው ፊት ለብሔራዊ ምክር-ቤቱ (ሸንጎው) በማቅረብና ስለ ሰውየውም ማንነት፣ ብቃትና ችሎታ በዝርዝር በማስረዳት ለውድድር ያቀርባል። የሸንጎ አባላትም በምስጢር ድምፅ አሰጣጥ ሥነ-ስርዓት ምርጫውን ይፈጽማሉ። በዚኽ መሠረት ለሊቀ መንበርነት ከመኢአድ (ምንም እንኳን በቦታው ባይኖሩም) ኢ/ር ኃይሉ ሻውል፣ ከኦብኮ ዶ/ር መረራ ጉዲና፣ ከአማራጭ-ኃይሎች ዶ/ር በዬነ ጴጥሮስ፣ ከኢዴፓ ዶ/ር አድማሱ ገበየሁ እና ከደቡብ-ኅብረት አቶ ሙሉ መጃ ለውድድር ቀርበው፤ ዶ/ር በዬነ ዘጠኝ ድምፅ፣ ዶ/ር መረራ ስምንት ድምፅ፣ ኢ/ር ኃይሉ ስድስት ድምፅ፣ ዶ/ር አድማሱ አምስት ድምፅ፣ አቶ ሙሉ ሁለት ድምፅ ስላገኙ፣ አብላጫ ድምፅ ያገኙት ዶ/ር በዬነ ጴጥሮስ የኅብረቱ ሊቀ-መንበር ሆነዋል። በመቀጠልም ለዋናው ጽ/ቤት ምክትል ሊቀ-መንበርነት ድርጅቶቹ ከዶ/ር በዬነ በስተቀር በመጀመሪያው ዙር ከቀረቡት ተወዳዳሪዎች መኻል በተመሣሣይ የድምፅ አሰጣጥ ሥርዓት ዶ/ር መረራ አሥራ-ሦስት ድምፅ፣ ዶ/ር አድማሱ

ዘጠኝ ድምፅ፣ አቶ ኃይሉ ስምንት ድምፅ በማግኘት አብላጫ ቁጥር ያገኙት ዶ/ር መረራ ጉዲና በአገር-ውስጥ ባለው ዋና ጽ/ቤት የኅብረቱ ምክትል ሊቀ-መንበር ሆነው ተመርጠዋል፡፡ ከዚያም ለዋና-ፀሐፊነት በተደረገው ውድድር መኢአድ የኢ/ር ኃይሉን ስም በፍላጎቱ ከተወዳዳሪነት ስላነሣ በእጩነት ከቀረቡት መኻል ዶ/ር አድማሱ ሃያ-ስምንት ድምፅ፣ አቶ ሙሉ ሁለት ድምፅ በማግኘት ዶ/ር አድማሱ ገበየሁ የኅብረቱ ዋና ፀሐፊ እና አቶ ሙሉ መጀ እረዳት ዋና-ፀሐፊ በመሆን፣ በውጭው ጽ/ቤት አቶ ፋሲካ በለጠ የኅብረቱ ምክትል ሊቀ-መንበርና መቶ አለቃ አያል ሰው ደሴ የኅብረቱ ምክትል ዋና-ፀሐፊ ሆነው በምርጫ ተሰይመዋል፡፡

በመዋቅሩ ውይይት ላይ ሌላው ስምምነት የተደረገበት ነጥብ የአመራር ሰጭውን ክፍል የሥራ ዘመን በተመለከተ ነበር፡፡ የመዋቅሩን ንድፍ ያዘጋጀው ክፍል ኃላፊዎችን በተመለከተ ያቀረበውና ጉባዔውም ተወያይቶ ያፀደቀው፤ አንደኛ የሊቀ-መንበሩና የምክትል ሊቀ-መናብርቱ የሥራ ዘመን በስድስት ወራት እንዲገደብ፣ ሁለተኛ አተካኩም ከስድስት ወራት በኋላ ምርጫ እየተካሄደ ሣይሆን በሊቀ-መንበሩና በዋናው ጽ/ቤት በሚገኘው ምክትል ሊቀ-መንበር መኻል ዝውውር እንዲደረግ በማድረግ ይሆናል፡፡ ይኸ ስሊት ወደ-ኋላ ላይ እንደምናየው ኅብረቱ ምርጫ-ዘጠና-ሰባትን የሰላማዊ ትግሉ አካል አድርጎ በመታገያ ስልትነት ሊያስተናግደው ሲወስን ገዥውን ፓርቲና መንግሥት ትርጉም ወዳለው ድርድር በማምጣት ምርጫው ነፃና ርቱኣዊ እንዲሆን ማድረግ ካልተቻለ የሚከተለውን እርምጃ ለመወሰን ሸንጎው በዓመት ውስጥ መሰብሰቡ የግድ መሆኑን በማጤንና ውሳኔውም ስለ-ነበር፣ በዚያ ጉባዔ ላይ ከአንድ ዓመቱ ሂደት ከተገኘው ልምድ በመነሣት የአመራሩን ጉዳይ መልሶ ለማየት ይችላል ከሚልም እምነት በመነሣት የተፈጸመ ነበር፡፡

የሊቀ-መንበርነቱን ኃላፊነት በአገር-ውስጥ በሚገኙ ድርጅቶች መኻል በየስድት ወራት እንዲዘዋወር የነበረው አሣብና ውሳኔም የተደረገው ቀደም-ሲል ከነበሩ ልምዶችና ካለው ሁኔታ በመነሣት ነበር፡፡ በብዙ ድርጅቶች ዘንድ የድርጅት መሪነትን እንደ ቋሚ የግል ንብረት የመቁጠርና የዕድሜ-ልክ ሹመት ተደርጎ መወሰዱ እየታየ መሆኑ መክሰም ያለበት አደገኛ ይዞታ መሆኑ ለብዙዎች ግልጥ ነው፡፡ ያ ደግሞ በተለይ የጋራ ትግሉን አሽመድማጅ ከሆኑት ምክንያቶችና፣ መቀጨት ያለበት አዝማሚያና መንጠፍ ያለበት የአምባ-ገነኖች መብቀያና ማቆጥቆጫ አንደኛው መስክ ነው፡፡ ምናልባትም በአንዳንድ ወገኖች ዘንድ በአለው ሁኔታ የድርጅት መሪነትን በአዘቦታዊና በተደላደለ ሁኔታ ከሚያዝ የፖለቲካ ሥልጣን ጋር የማምታታት ሁኔታ ሊኖር ይችላል፡፡ በአሁኑ ጊዜ የአንዳንድ ድርጅቶችን የአመራር ይዞታና ሁኔታ ስናይ ምናልባትም የአመራር ቦታን በተደላደለ ሁኔታ ለግል እውቅናንና ዝናን ወይም ሌሎች ቁሣዊ ጥቅማጥቆችን ለማስገኘት የሚያዝና የሚሰጥ ሹመት አድርጎ የመቁጠር አባዜ ያለ ይመስላል፡፡ ያም የትግሉ ተፈጥሮኣዊ ባኅሪ ላይ ካለ ያልተሟላ ወይም የተዛባ አመለካከት የመነጨ ሊሆን ይችላል፡፡ ምናልባትም የአምባ-ገነን አዙሪቶችን ሂደት ለመበጠስና የሥርዓት ለውጥ ለማምጣት በሚደረግ ትግል ወቅት የሚሰጥ ማንኛውም ኃላፊነት አደራው እጅጉን የበዛ፣ ታግሎ-አታጋይነትና መስዋዕትነትን የሚጠይቅ ከባድ ዕዳ መሆኑን በአንዳንድ ወገኖች ዘንድ በውል ግንዛቤ ስላልተወሰደበት ሊሆንም ይችላል፡፡ *(በጉዳዩ ላይ በመጨረሻው "አመራር" በሚለው ክፍል ትንሽ ዘርዘር አድርጌ ለማሣየት ሞክሬአለሁ፡፡)*

ኅብረቱም ሲመሠረት የአገራችንን ሁኔታ ለመቀየር በሚደረገው የሥርዓት ለውጥ ትግል የበላይ አመራሩን እንዲይዙ ክብሩ የተሰጣቸው ወገኖች ለተወሰነ ጊዜ በየስድት ወራት እንዲቀያየሩ ማድረጉ፣ እነሱ ከማንኛውም ታጋይ አባል የተለዩ ሣይሆን ትግሉን ለማስተባበር <u>አደራ</u> የተሰጣቸው መሆኑን እንዲገነዘቡና በተሰጣቸው ጊዜ ውስጥ የችሎታቸውንና ያቅማቸውን እንዲያደርጉ የተሻለ ሊያተጋቸው ይችላል ከሚል እሣቤ ነው፡፡ በተጨማሪም በአገራችን፣ በተለይም በዘመነ-ኢሕአዴግ የተፈጠረው የድርጅቶች እንደ አሸን መፍላታና ምስቅልቅሉ የወጣው የድርጅቶች ያለፈ ታሪክ ባስከተለው በበቂ አለመጣጣም፣ አለመተዋወቅና አለመተማመን ምክንያት አንዱ አስቸጋሪ ጉዳይ የሁሉንም ቀርቶ የአብዛኛውን አመኔታና ከበሬታ ሊያተርፍ የሚችል አመራር ማግኘት ያለመቻል ጉዳይ ነው፡፡ ይኸ ደግሞ በተለይ የብዙዎችን አስተሣሰብ ኮድኳጅና ቀያጅ የሆነው ብሔረ-ሰብን (ጎሣን) መሠረት ያደረገው አዲሱ ፖለቲካዊ የአደረጃጀት ዘይቤ ሁኔታውን ይበልጥ አወሳስቦታል፡፡ ስለሆነም አመራሩ በአጫጭር ጊዜዎች እንዲቀያየር መደረጉ በድርጅቶችም

ይሁን ኃላፊነት በተሠጣቸውና በቀሩት መኻል የተሻለ መተዋወቅ እንዲኖር፣ በአጉል ጥርጣሬ ላይ የተመሠረቱ ልዩነቶችም እንዲጠብቡና መተማመንንም ቀስ-በቀስ ለማዳበር የበለጠ ዕድል ሊሰጥ፤ ያም ሲሆን ለአንዳንዶችም ቅይዳቸውን ለመፍታትና እራሣቸውን ካገቱበት ውሱን ክትር ሰብረው ለውጣት የተሻለ አጋጣሚን ሊፈጥርላቸው ይችላል ከሚል ቀና እምነት ነው:: ያ አካሄድም ክፍተቱን መድፈን ያቃተውን የአመራር ችግር ለመወጣትና መከባበር፣ መግባባትንና በመተማመን ላይ የተመሠረተ ሠፊ አመለካከት ያለውና ቁርጠኛ አመራር ለማውጣት ዕድል ይሰጣል ከሚል እንደተደረገ ግልጥ ነው::

ጉባዔው መዋቅሩንና አርማውን አፅድቆ ሸንጎውን ከሰየመና አጠቃላይ መርኅ-ተከል መመሪያውን ለሸንጎው በመስጠት ሲጠናቀቅ፣ ሸንጎው ሥራ-አስፈጻሚውን፣ ማዕከላዊ-አመራሩንና የተግባር ኮሚቴዎችን ኃላፊዎች በምርጫ በመሰየም ለሥራ-አስፈጻሚ ኮሚቴው ዝርዝር መመሪያዎችን በመስጠት፣ መተዳደሪያ-ደንቡን፣ የኅብረቱን አጠቃላይ ራዕይና የሚታገልባቸውን ሕዝባዊ ዓላማዎች ባካተተ መልክ ብሔራዊ የፖለቲካ መርኃ-ግብር (ፕሮግራም) እና የኤኮኖሚ አማራጭ መርኃ-እቅድ (ፖሊሲ) እንዲሁም ሌሎች ተዛማች ሰነዶችን እንዲያወጣ፣ በኅብረቱ ራዕይ ማእቀፍ ውስጥ የአጭር-ጊዜ፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ የሥራ እቅዶችን በመተለም ተግባራዊ እንቅስቃሴውን በቶሎ እንዲጀምር፣ ወዘተ... በመወሰን ኃላፊነቱን ለየሚመለከተው እርከን አስተላልፏል::

በዚሁ መሠረት ኃላፊነቱን የተረከቡት ወገኖች ምንም ጊዜ ሳይባክኑ በቀጥታ ነው ወደ-አጠቃላይ እንቅስቃሴው የገቡት:: ሥራ-አስፈጻሚው አካል ወዲያውኑ የአቋም መግለጫ በማውጣት፣ በማግስቱ ደግሞ ተሰብስቦ የተግባር ኮሚቴዎችን ማሟላትና ከመተዳደሪያ-ደንቡ ጀምሮ ያሉ ሰነዶችን በማዘጋጀቱ ረገድ ከሌሎች ተዛማች የአደረጃጀት ሥራዎች ጋር አዳምሮ ያለ እረፍት በመሥራት የተጣለበትን ኃላፊነት ለመወጣት ሞክሯል:: በመጀመሪያ ካደረጋቸው ተግባሮች ውስጥ ገንዘቡን፣ አቅሙንና እውቀቱን አስተባብሮና ለግሦ ጉባዔው በተሣካ ሁኔታ እንዲካሄድ ላስቻለው ኅብረተሰብ ሕዝባዊ ስብሰባ በመጥራት ኅብረቱን ማስተዋወቅ ነበር:: ስለሆነም ጉባዔው በሐምሌ ሃያ-ስድስት ቀን ዘጠና አምስት ዓ/ም ተጠናቅቆ በሁለተኛው ቀን እሁድ ሐምሌ ሃያ-ስምንት ቀን ዋሽንግቶን ዲሲ በሚገኘው ዋርድማን ፓርክ ማሪዮት ሆቴል ውስጥ ታላቅ ሕዝባዊ ስብሰባ በመጥራት ኅብረቱንና ዓላማውን፣ አባል ድርጅቶቹንና ኃላፊዎቹን ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር አስተዋውቋል:: ጉባዔ አዘጋጅ ኮሚቴው ከመጀመሪያው እንዳቀደውም የየድርጅቱ የልዑክ ቡድን ወደ-ጉባዔ ከመግባቱ በፊት የሕዝብን ጉጉትና ጥያቄ የሚመልስና አገርን የሚታደግ የጋራ አካል መሥርተው ለመውጣት ያላቸውን ዝግጁነትና ቁርጠኝነት ጥሪ በተደረገላቸው ታዋቂ ኢትዮጵያውያን ፊት ቃል እንዲገቡ እንደተደረገው ሁሉ፣ ጉባዔው እንደተጠበቀው ኅብረቱን መሥርቶ ሲወጣ ደግሞ እያንዳንዱ መሥራች ድርጅትና ኃላፊነት የተሰጣቸው ወገኖች ተቻችለውና አንድነታቸውን ጠብቀው በስንት ምጥ የተወለደውን ኅብረት ለፍሬ እንደሚያበቁት በሕዝብ ፊት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ቃል እንዲገቡ ተደረገ::

ኃላፊነት በተሰጣቸውና በየድርጅቱ ተወካዮች አማካይነትም *"ከእንግዲኽ ልዩነት አክትሟል፣.. መንገዳችን በጋራ ነው፣.. ለኢትዮጵያ ትንሣዔ፣ ለአዲስ ዴሞክራሲያዊና ሕዝባዊ ሥርዓት እውን መሆን እስከ-መጨረሻው በዚኽ ኅብረት ሥር በአንድነት እንታገላለን፣ ወዘተ.. "* የሚሉ የተስፋና የቁርጠኝነት መልዕክቶች ተስተጋቡ:: በጉባዔው መክፈቻ ሥነ-ሥርዓት ላይ ታዋቂ ኢትጵያውያን ልብ የሚነኩ የማበረታቻና የአደራ መልእክቶቻቸውን እንዳስተላለፉ ሁሉ *(Tsegaye G.Medhin, HibretMisreta.pdf) በዚኽ ምስራች-አብሣሪ ሕዝባዊ ስበሰባ ላይም ወኔ-ቀስቃሽና 'አይዟችሁ በርቱ' መልእክቶች ተላልፈዋል:: *(AssefaGeMariam,Hibret Misreta238.pdf) ከዚያም በኋላ በስልክ፣ በፋክስ፣ በኢ-ሜይል፣ በፊት-ለፊት ግንኙነት፣ ወዘተ.. ለኅብረቱ የሚተላለፉ የደስታና የ'አደራችሁን በርቱ!' መልእክቶች በርካታና በአጠቃላይም በወቅቱ የነበረውን የሕዝብ ስሜትና ተስፋ የሚያንፀባርቁ ነበሩ:: ኃላፊነት የተሰጣቸው ወገኖችም ያሣዩት የጋለ ሥነ-ልቦናዊ ዝግጁነትና ፍላጎት፣ ተግቶ የመሥራት ጉጉትና ቁርጠኝነት እጅግ አበረታች ነበር:: የእንኳን ደስ-አላችሁ መልእክቶችም ከውጭ-አገር መንግሥታት ወኪሎችና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካሎች ጭምር ይተላለፉ ነበር::

***በክፍል አሥራ-ስምንት ይቀጥላል....***